# የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ግምገማና እና ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 1-10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

## ከኖቬምበር 11-20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኖቬምበር 2021
አዲስ አበባ

**ርዕስ** **ገፅ**


እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ....1

ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ....2

ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት....3

ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን....4

ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር....4

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ....5

በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ....5

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....5

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታበውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ...6

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ....6

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር....7

ሁኔታ አዝማሚያ....7

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ....7

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ....8


# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ደረቅ፣ ፀሃያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በአብዛኞዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አመዝኖ የተስተዋለ ቢሆንም፤ ከአስሩ ቀን አጋማሽ በኋላ ግን ወደ አገራችን ይገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር ከዕለት ወደ ዕለት በመጨመሩ በተለይም በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን ተስተዉሎባቸዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም በአንዳንድ የምዕራብ አማራ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ የምዕራብና ጥቂት የደቡብ ኦሮሚያ፣ የጋምቤላ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ የሲዳማና የደቡብ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በመጨረሻዎቹ አምስት ቀናት ከቀላል እሰከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ነበራቸዉ፡፡ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በደምቢዶሎ 66.2፣ በጋምቤላ 51.4፣ በወላይታ ሶዶ 51.4፣ በብላቴ 51.4፣ በጠርጫ 42.5፣ በቦሬ 37.0፣ በጊምቢ 34.7፣ በማሻ 30.6 እንዲሁም በአልጌ 30.0 በሚ.ሜ ይገኙባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከነበረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በአንፃራዊ ሁኔታ ቀንሶ ተስተዉሏል፡፡


ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም በአንዳንድ የምዕራብ አማራ፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፤ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በጅማ እንዲሁም በአርሲና ባሌ ዞኖች ምዕራባዊው ክፍል፤ ከጋምቤላ ዞን የመዠንገርና የአኝዋክ ዞኖች እንዲሁም በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ላይ ከ5-80 ሚሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-8 ቀናት ያህል የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

በዚህም መሠረት ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በምዕራብ አማራ፤ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ሁሉም ዞኖች፣ በቄለምና ምዕራብ ወለጋ፣ በኢሉአባቦራ፣ በምስራቅ ወለጋ፣ በሞያሌ እንዲሁም በአርሲና ባሌ ዞኖች ምዕራባዊው ክፍል፤ ከጋምቤላ ዞን የመዠንገርና የአኝዋክ ዞኖች እንዲሁም በአብዛኛው በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ላይ መደበኛና ከመደበኛው በላይ የዝናብ መጠን የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ ሆነው ሰንብተዋል (ካርታ 3)፡፡


ካርታ 1   ኢ.ሌ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 3 ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቨምበር ወር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ተስተውሏል። ይህም ሁኔታ በዚህ ጊዜ የሰብል ስብሰባቸውን በሚያካሂዱ በአንዳንድ ሰብል በደረሰባቸው አካባቢዎች ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በሌላ በኩል የደቡብ፣ የደቡብ ምዕራብና የምዕራብ ኢትዮጵያ እንዲሁም ጥቂት የአማራ ክፍሎች በአንዳንድ ቦታዎቻቸው ላይ ዝናብ ነበራቸው። ይህም ሁኔታ ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም በመኸር ወቅት መጨረሻ ላይ በአፈር ውስጥ በተከማቸ እርጥበት በመታገዝ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው። እንዲሁም የማለዳውና የሌሊቱ ቅዝቃዜ እምብዛም ያልተጠናከረ እንደነበር ተስተዉሏል (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 01-10 ኖቭምበር 2021 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ በተመለከተ ከመጠነኛ እርጥበማ እስከ እርጥበታማ ሁኔታ በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ተስተውሏል፡፡ ይህንን ሁኔታ ተከትሎ በአብዛኛዉ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ገናሌዳዋ"  የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በጥቂት የላይኛዉና የታችኛዉ አባይ፣ የላይኛዉ ተከዜ ተፋሰሶች ከከፍተኛ እርጥበት እስከ መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ከፊል ደረቅ እና ደረቅ ሁኔታ ተስተውሎባቸዋል (ካርታ 5) ፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2021 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይጠበቃል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ የመካከለኛው እና የደቡበ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ ባሉ ቀናት ውርጭ የማስከተል ጥንካሬ ሊኖረው ይችላል፡፡

በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ አጋማሽ ላይ መጠነኛ የደመና ሽፋን እና በጥቂት ቦታዎች ላይም ቀላል መጠን ያለው ዝናብ ይጠበቃል፡፡

በአጠቃላይ <u>ከኦሮሚያ ክልል ኢሉአባቦራ፣ ሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ ጥቂት የአርሲ፣ የጅማ እና የጉጂ ዞኖች፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የከፋና የቤንች ማጂ፣ የጋሞ፣ የጎፋ፣ የወላይታ እና የጌዲዮ ዞኖች እንዲሁም የሲዳማ ክልል በተለያዩ ሥፍራዎቻቸው ላይ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የደቡብ ጎንደር፣ የምዕራብና የምስራቅ ጎጃም ጥቂት ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ የመዝነብ ዕድል ሊኖር ይችላል፡፡</u>

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የኖቬምበር ሁለተኛው አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይና በአንዳንድ ቦታዎች ላይም የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ቀጣይነት እንደሚኖረው በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ ላይ ተመልክቷል፡፡ በተለይም የሚጠበቀው ደረቃማው የአየር ሁኔታ በመከናወን ላይ ለሚገኘው የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በአንጻሩም ከደረቃማውና ከነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ቅዝቃዜው በቀጣይነት እንደሚስተዋል የትንበያ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ እድገታቸውን ባልጨረሱ

በተለይም ፍሬ በመሙላት ላይ በሚገኙ ሰብሎች እንዲሁም በመስኖ በመታገዝ በሚለሙ በፍራፍሬ ተክሎችና በጓሮ አትክልቶች ላይ አሉታዊ ጎን ሊኖረው ይችላል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች እንደ አካባቢው ሁኔታ የሚኖረውን ቅዝቃዜ ለማሻሻል የሚረዱ የተለመዱ ተግባራትን ለማከናወን የበኩላቸውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ፡፡

በሌላም በኩል አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በደቡብ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ ሊገኝ የሚችለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውኃ ፍላጎት መሟላት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት ከማሻሻል አንፃር ጠቀሜታዉ የጎላ ሰለሆነ አርሶ አደሩና የሚመለከታቸዉ አካላት የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም የሚኖርባቸው ቢሆንም፣ የሚኖረው እርጥበታማ ሁኔታ በመኸር ሰብል ስብሰባና በድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባርት ላይ ጉዳት ሊይስከትል ስለሚችል የሚመለከታቸው አካላት የደረሱ ሰብሎችን በሚኖሩት ደረቅ ሰሞናት ለመሰብሰብ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ ከወዲሁ ይመከራሉ።

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11 እስከ 20/2021 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በዉሀዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በአንዳንድ በሰሜን ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በደቡብ አጋማሽ ላይ መጠነኛ የደመና ሽፋን እና በጥቂት ቦታዎች ላይ እርጥበታማ እና መጠነኛ እርጥበት ይጠበቃል፡፡

በዚህም መሰረት በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እንደሚያመዝን የሚጠበቅ ሲሆን፣ በሌላ በኩልም በአብዛኛው ባሮአኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ የመካከለኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ እና ኦሞጊቤ ተፋሰሶች ላይ እርጥበታማ እና መጠነኛ እርጥበት ሊያገኙ እንደሚችሉ ይጠበቃል፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ላይ ይቆያሉ፡፡ በመሆኑም በእነዚህ የበጋ ተጠቃሚ የሆኑ ተፋሰሶች ላይ የሚገኘው የእርጥበት መጠን በውሃው ዘርፍ ላይ ያሉ ተጠቃሚዎቻችን የሚገኘውን ውሃ በአግባቡ እንዲጠቀሙ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡